Washington State Department of CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

**(Washington Early Support for Infants and Toddlers (ESIT)) ፕሮግራም**

# ለግምገማ/ምዘና የሚሰጥ ማሳወቂያ እና ፈቃድ

**ዓላማ፡-** ግምገማ/ምዘና እንዲከናወን ሃሳብ የቀረበ እንደሆነ ለወላጅ(ጆች) በጽሁፍ ለማሳወቅ እና ግምገማውን/ምዘናውን ለማድረግ ከወላጅ ፈቀድ ለማግኘት።

| **የልጅ ሥም** | **የትውልድ ቀን** | **የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ** |
|---|---|---|
| | | |

**ማሳወቂያው የተሰጠበት ምክንያት**

ESIT የግምገማ እና የምዘና ተግባራትን ከማከናወኑ በፊት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ እንዲሰጥዎ ይገደዳል። ለእነዚህ ተግባራት ከዚህ በታች በሚያሰፍሩት ፊርማዎ አማካኝነት በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ የጽሁፍ ፈቃድ እንዲሰጡ ያስፈልጋል። የግምገማ እና ምዘና ዓላማ ከእርስዎ እና እርስዎ እንዲሳተፉ ከሚጠይቋቸው ሌሎች ሰዎች ስለ ልጅዎ መረጃ ማግኘት፤ ስለልጅዎ ዕድገት ለቤተሰብዎ ተጨማሪ መረጃ መስጠት፤ የልጅዎን ልዩ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች መለየት እና እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት አግባብ ሊሆኑ የሚችሉ አገልግሎቶችን መለየት፤ ልጅዎ ለ ESIT ፕሮግራም አሁንም ብቁ መሆኑን መወሰን፤ እና ልጅዎ አሁንም ብቁ ከሆነ፤ በእርስዎ ስምምነት እና ተሳትፎ፣ በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) በጽሁፍ ለማዘጋጀት ወይም ለማሻሻል ነው። ይህ ያንን ማሳወቂያ በተመለከተ ለእርስዎ የተሰጠ መግለጫ ነው።

*"ፈቃድ" ሰጥተዋል ማለት፡- ( (1)ፈቃድዎ ከተጠየቀባቸው ተግባራት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም መረጃዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ (ይህንን ለማድረግ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ካልሆነ በስተቀር) ወይም እንደ አግባብነቱ የምልክት ቋንቋን፣ብሬልን ወይም የቃላት ተግባቦትን ጨምሮ በሌላ የተግባቦት መንገድ ሙሉ በሙሉ ማግኘትዎን። (2)ፈቃድዎ ስለ ተጠየቀባቸው፤ ተግባራት ተረድተው እነዚህን ለማከናወን በጽሁፍ ፈቃድ መስጠትዎን (3) ፈቃዱ የሚከናወኑትን ተግባራት እና ለሌሎች ሰዎች የሚሰጡትን ማህደሮች (ካሉ) ለማን እንደሚሰጡ ጨምሮ ይዘረዝራል፤ እና (4) ፈቃድዎን የሰጠሁት በፈቃደኝነት መሆኑን እና በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ በማሳወቅ ሊያነሱት እንደምችሉ መረዳትዎን። ፈቃድዎን ካነሱ፣ ወደ ኋላ የሚሰራ አይሆንም* (ማለትም፣ ፈቃዱ ከመነሳቱ በፊት ለተወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች አያገለግልም)።

**እንዲወሰድ የቀረበ እርምጃ**

ከሁለት የተለያዩ የስራ ዘርፎች በመጡ ቢያንስ ሁለት ብቃት ያላቸው ግለሰቦች(ወይም በሁለት ዘርፎች ብቃት ባለው አንድ ባለሙያ) በ ESIT ፕሮግራም ፖሊሲዎች እና ሥርዓቶች መሰረት ግምገማ እና ምዘና ይከናወናል። እንደ ግምገማው ቡድን አባልነት የእርስዎ ተሳትፎ በእጅጉ ይበረታታል። ልጅዎን በተሻለ ስለሚያውቁት ስለልጅዎ ወሳኝ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ። ግምገማ እና ምዘናው ልጅዎ በአእምሮ፣ በአጠቃላይ እንቅስቃሴ፣ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እንቅስቃሴ፣ በተግባቦት፣ በማህበራዊ-የስሜት እና ራስን የማላመድ ዕድገት፣ እንዲሁም በዕይታ እና በመስማት ምን ያህል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በተሟላ ሁኔታ መመልከት ነው። ውጤቶቹ ልጅዎ በሁሉም ዘርፎች ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እና የ ESIT አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ነው አይደለም የሚለውን ያመላከታሉ።

**መግለጫ**

የሚሚቀርበው ግምገማ በርካታ ቅደም ተከተሎችን የሚያካትት ሲሆን ከእነዚህም መካከል የግምገማ ሰነድን ማስተዳደር፣ የልጁን ታሪድ፣ ወላጅ(ጆማነጋገር፣ ከሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ ከተንከባካቢዎች ወይም ከሌሎች የሕክምና ወይም ሌላ ሙያተኞች መረጃ መሰብሰብን እንዲሁም የሕክምና፣ የትምህርት እና ሌሎች ማህደሮችን መመልከትን ያካትታል። የሚቀርቡት የምዘና ቅደም ተከተሎች የልጅዎን ልዩ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች እና አግባብ የሆኑ የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይወስናሉ። ምዘና የሚያካትተው፡-የግምገማ ውጤቶችን መከለስ:- የግል ምልከታ በልጁ ላይ በማድረግ ግላዊ በመደበኛ እና ኢ-መደበኛ የምዘና ቅደም ተከተሎችን በመጠቀም በእያንዳንዱ የዕድገት ክልል ላይ የልጁን ፍላጎቶች መለየት። ለዚህ ግመግማ እና ምዘና የሚጠቀሟቸውን ዘዴዎች በተመለከተ የ ESIT አገልግሎት ሰጪዎች ከእርስዎ ጋር ይነጋገራሉ። ግምገማው እና ምዘናው እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ ይከናወናል። ውጤቶቹም በልጅዎ የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ ማህደር ውስጥ ይቀመጣል። እርስዎ ያንን ለማድረግ በጽሁፍ ፈቃድዎን ካልሰጡ በስተቀር የትኛውም መረጃ ከ ESIT ፕሮግራም ውጪ ላለ ማንኛውም ሰው ወይም ኤጀንሲ አይሰጥም። የ IFSP ቡድን ልጅዎ ብቁ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑን ይወስናል ፣ እናም የብቁነት ውነውን ለመቃወም ያለዎትን መብት ጨምሮ የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይሰጥዎታል።

*የወላጅ ሥም*
*የመጀመሪያ ፊደል*

| |
|---|
| |

***ማረጋገጫ እና የፈቃድ መግለጫ***

***ከዚህ ማሳወቂያ ጋር የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናትን የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ ፕሮግራም፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ የሥኑ-ስርዓት ጥበቃዎችን [የወላጅ መብት]) ቅጂ ደርሶኛል።***

እነዚህ መብቶች እና የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች ተብራርተውልኝ እኔም ተረድቻቸዋለሁ። ፈቃዴ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የተሰጠ መሆኑን እና ይህን ቅጽ ከፈረምኩኝ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ልጄ እንዳይገመገም ማድረግ የምችል መሆኑን ተድቻለሁ። ለዚህ ግምገማ ወይም ምዘና ፈቃድ መስጠት ካልፈለግኩኝ፣ ልጄ እንደማይገመገም ወይም ምዘና እንደማይደረግለት ተረድቻለሁ።

| |
|---|
| ☐ ፈቃዴን እሰጣለሁ ☐ ፈቃዴን አልሰጥም |
| የESIT ፕሮግራም ከላይ የተገለጹትን ተግባራት እንዲያከውን ወይም እንዳያከናውን በመረጃ ላይ የተመሰረ ፈቃድ። |

ፌብሩዋሪ 2012

| | |
|---|---|
| **የወላጅ(ጆች) ሥም** | |
| **የወላጅ(ጆች) ፊርማ** | **ቀን** |
| **የተቀበለው ሰው ስም/ማዕረግ/ኤጀንሲ** | **ቀን** |

*አባሪ፦ የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናትን የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ የሥኑስርዓት ጥበቃዎች[የወላጅ መብት])*
*ማስታወሻ፦ ወላጆች የዚህ ቅጽ ግልባጭ የሚደርሳቸው ሲሆን የተፈረበመት ቅጂ ደግሞ በልጁ የጨቅላነት ጊዜ አገልግሎት ማህደር ውስጥ ይካተታል።*